| |
|---|
| ዘ LEAD ኢኖቬሽን ስቱዲዮ ምንድን ነው? |
| ለአንዳንድ ተማሪዎች፣ በፓርክ ሂል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለየት ያለ ነው። በ LEAD ኢኖቬሽን ስቱዲዮ ተማሪዎች በኪራይ በተያዘ ሕንጻ ውስጥ የአንድ ሙሉ ቀን የትምህርት ፕሮግራም ይሰጣቸዋል፤ በዚያም እንደሁኔታው ሊመቻች በሚችል፣ በግላዊ የትምህርት ከባቢ የሚማሩ ሲሆኑ፣ ትኩረት የሚደረገውም ችግር በመፍታት ክህሎቶች፣ በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ ትምህርት እና በሙያዊ ልምዶች ላይ ነው። በቀጣዩ የትምህርት ዘመን፣ ለ LEAD የራሱ ሕንጻ እንከፍታለን፤ ሕንጻውም ለዚህ ልዩ ዓላማ የተዘጋጀ ይሆናል። |
| ሁሉም የ LEAD ተማሪዎች በትምህርታቸው ዙሪያ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እገዛ የሚሰጧቸው አካላት አሉ። የ LEAD ተማሪዎች በትምህርታቸው ዙሪያ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሲሆን፣ መምህራን ደግሞ ተማሪዎች የሚያስልጋቸውን ድጋፍ ሁሉ ይሰጣሉ። ወቅታዊ ቴክኖሎጂ ደግሞ ተማሪዎች በመምህራን አስተባባሪነት የግል ግቦቻቸውን እንዲያሟሉ ያግዛቸዋል። |
| የትኞቹ ተማሪዎች የ LEAD ኢኖቬሽን ስቱዲዮን ይከታተላሉ። |
| የትምህርት ቤቱ የሚከተለው ለእያንዳንዱ ተማሪ እንደ ፍላጎቱ የማስተማር ስልት የተለያየ የኋላ ታሪክ፣ ፍላጎት እና ግብ ላላቸው ተማሪዎች ምቹ ነው። በ2020-2021 የትምህርት ዘመን ማንኛውም ተማሪ የ LEADን ትምህርት መከታተል የሚችል ሲሆን፣ ይህም በዲስትሪክቱ የተማሪውን ብዛት የሚያንጸባርቅ ነው። ፕሮግራሙ በተማሪዎች ግላዊ ፍላጎቶች ላይ ያተኮረ መሆኑ 504 እና IEP ላላቸው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሰልጣኞች እና ተማሪዎች |
| በ LEAD የትምህርት ክፍሎች ምንም ይመስላሉ? |
| የ LEAD ተማሪዎች ሁለቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻችን የሚሰጡትን ትምህርት ይከታተላሉ። ሆኖም ግን የምንከተለው የትምህርት አሰጣጥ ሞዴል በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ፣ በችግሮች ዙሪያ እና ከሙያ ትምህርት መቅሰም (PBL) እና የግል ፍላጎትን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው። ተማሪዎች በመደበኛነት ከምክር ሰዎች ጋር በግል በመገናኘት፣ ግብ እንዲወስኑ እና ክህሎቶቻቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ እናግዛቸዋለን። |
| በ LEAD የተማሪዎች ሕይወት ምን ይመስላል? |
| ተማሪዎች ሁሉንም ትምህርቶች በ LEAD ኢኖቬሽን ስቱዲዮ ይከታተላሉ፤ ይህም ሆኖ አሁንም የፓርክ ሂል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትሮጃኖች እና የፓርክ ሂል ሳውዝ ፓንተርስ ሆነው ይቀጥላሉ። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በተጓዳኝ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ በባንድ፣ በስፖርት እና በዳንስ ይሳተፋሉ። እንዲሁም LEAD ልዩ ልዩ ክለቦች እና እንቅስቃሴዎች እንዲሁም የትምህርት ቤት መንፈስ ለመፍጠር ስብሰባዎች እና ዕድሎች ለተማሪዎች ይሰጣሉ። |
| LEAD ከማኅበረሰብ ጋር ትስስር በመፍጠር ላይ ትኩረት ያደርጋል - በዚህም ሥር የ LEAD ማኅበረሰብ፣ የፓርክ ሂል እና የፓርክ ሂል ሳውዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማኅበረሰቦችን ያካትታል። የ LEAD ተማሪዎች ከአካባቢያዊ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር በስፋት ይሰራሉ፤ በፕሮጀክት ሥራ ላይ ትኩርት በሚያደርጉ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋሉ። |
| LEAD የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣልን? |
| አዎ፣ የፓርክ ሂል ትምህርት ቤት ዲስትክት ለሁለቱም ተማሪዎች ትራንስፖርት ይሰጣል። |
| ጥያቄዎቼ ምላሽ የሚያገኙት እንዴት ነው? |
| እባክዎን በስልክ ቁጥር (816) 359 – 4130 በመደወል ጥያቄያችሁን አቅርቡልን፤ እንዲሁም ከመረጃ መስጫ ምሽቶች መካከል በአንዱ ለመሳተፍ ዕቅድ ይያዙ። እንዲህ ስላሉት ምሽቶች በድረ ገጻችን lead.parkhill.k12.mo.us መረጃ ማግኘት |

| |
|---|
| ትችላላችሁ። |
| ተማሪዎች የሚያመለክቱት እንዴት ነው? |
| ሁለቱም ተማሪዎች በመደበኛ የምዝገባ ሂደት በ LEAD ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፉ እንጋብዛለን። |
| ፓርክ ሂል ስኩል ዲስትሪክት 7703 NW Barry Road Kansas City, MO 64153 |
| ኢኖቬሽን ስቱዲዮ |
| መምራት፣ ብቃት መስጠት፣ ማበርታት እና ማለም |
| LEAD |